No. 3 - January 2011

European Union

caritas international

# Quarterly UPDATE

ECC-SADCO

# በምግብ ራስን መቻል፡- እነሞር እና ምዕራብ ባዴዋጮ ወረዳዎች የደካማ አርሶ አደሮች የግብርና ምርት አቅም ማስፋፊያ

## መግቢያ

እ.ኤ.አ ከታህሳስ 2010ዓ.ም ጀምሮ የምግብ ዋጋ ማሻቀብን አስከትሎ በአለም አቀፍ ደረጃ አፋጣኝ እርምጃን ለመውሠድ የተቀረፀው በምግብ ራስን ማስቻል ፕሮጀክት በአውሮፓ ህብረት እና ካሪታስ ቤልጂም የገንዘብ ድጋፍ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን በማህበራዊ ልማት ኮሚሽን በእምድብርና ሶዶ ሀገረስብከት አስተባባሪነት የቤተሠብን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ አጠቃላይ እቅድ አውጥቶ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡ በተለይም ደግሞ ፕሮጀክቱ 6,900 ለሚሆኑ ደሀ አባወራዎች በ15 ቀበሌዎች የምግብ አቅርቦትን አቅም ለማሳደግ ድጋፍ ይሠጣል፡፡ ፕሮጀክቱ ከታቀደበት ጊዜ አንስቶ አጋር ድርጅቶች እና ድጋፍ ሰጪ አካላት የፕሮጀክቱ እቅስቃሴ ወደፊት እንዲቀጥል ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ የዚህ ፕሮጀክት ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ አስችሏቸዋል፡፡

ፕሮጀክቱ በሶስት እንቅስቃሴዎችና ውጤቶች ላይ መሰረት ያደረገ ነው፡፡

| | |
|---|---|
| 1 | የ3,861 አባወራዎች አመታዊ የሰብል ምርትና የማምረት አቅምን ማሳደግ |
| | ▪ የመስኖ ልማት ማሳደግ<br>▪ አነስተኛ የዘር ማባዛትንና የዘር ባንክን ማቋቋም<br>▪ የእርሻ መሬትን ከአፈር መከላትና ከዝናብ እጥበት መከላከል |
| 2 | የ6,560 አባወራዎችን የከብቶች እርባታና ምርት ማሳደግ |
| | ▪ ምርታማ የሆኑ የአገር ውስጥ ፍየሎች አቅርቦት<br>▪ በምርት አቅማቸው የተሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችን ማሳደግ<br>▪ የእንሰሳት መኖና ውሀ አቅርቦት<br>▪ የእንሰሳት ህክምና አገልግሎትን ማጎልበት |
| 3 | ለአርሶ አደሮች የኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን ጥራት ማሳደግ |
| | ▪ ለአርሶ አደሮቹ የስልጠና ማዕከላትን መገንባት<br>▪ አርሶ አደሮችንና የልማት ስራ ሠራተኞችን ማሰልጠን<br>▪ መረጃ ፣ትምህርት እና የግንኙነት አቅምን ማሳደግ |

ባላቸው ውስን የመሬትና የከብቶች ሀብት መጠን ደሀና እጅግ በጣም ደሀ የሆኑ 6,900 አባወራዎች በ1,111,456.08 ዩሮ ኢንቨስትመንት በቀጥታ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ እንዲሁም መካከለኛና የተሻለ ገቢ ያላቸውን ጨምሮ 10,028 አባወራዎች ወይም 50,140 ግለሰቦች ህብረተሰብ አቀፍ በሆነው ፕሮግራም ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

ፕሮጀክቱ በሚያበቃበት እ.ኤ.አ በጥቅምት 2011 የምግብ ዋስትናቸው ያልተረጋገጠ አባወራዎች የምግብ ዋስትናቸው ከመረጋገጡም በላይ የነፍስ ወከፍ ገቢያቸው (በቀጥታ ከምርታቸው ተጠቃሚ የሆኑ) እንዲሁም የቀንድ ከብት እሴታቸው በእጥፍ ያድጋል፡፡

**ክንውኖች**፡- ከጥቅምት እስከ ታህሳስ 2010ዓ.ም

## የሠብል ምርትና ምርታማነት

የዘር ማባዛት እንቅስቃሴው የተሻሻለ የድንች ዘር፣ የጤፍና የስንዴ ምርትን ለማሳደግ አስችሏል፡፡ በተደረገው ስምምነት መሠረት አርሶ አደሮቹ 120% የሚሆነውን ዘር ለሚቀጥለው ጊዜ እንዲጠቀሙበት ተመላሽ አድርገዋል፡፡ የዘር ባንክ ግንባታና የስራስር ዘር ባንክ ግንባታዎች እየተከናወኑ ቢሆኑም ጊዜያዊ ማጠራቀሚያ ተዘጋጅቷል፡፡ 133 ተጠቃሚዎች በዘር ባንክ አስተዳደር ላይ ስልጠና ተካፍለዋል፡፡ የመስኖ ስራ ግንባታ ለማከናወን የስራው ተቋራጭ ተመርጧል፡፡ በእጅ የሚሰሩ አነስተኛ የመስኖ ውሀ ፓምፖች በአነስተኛ ብድር እንዲያገኙ ተመቻችቷል፡፡ በመጨረሻም ተጠቃሚዎች(155) በአፈር ውሀና ጥበቃ÷በማፋሰሻ ቱቦዎች ግንባታና ጥገና ላይ ስልጠና ወስደዋል፡፡

**ከብቶች**፡- 147 ፍየሎችና 520 በጎች ለ996



ስዕል.1 የተሻሻለ የጤፍ ዘር ምርት



ስዕል.2: የአፈር ውሀና ጥበቃ ስራ

ተጠቃሚዎች ተከፋፍሏል፡፡ 183 ስልጠና ወስደዋል፡፡ የተሻሉ ዝርያ ያላቸው14 ኮርማዎችን ፕሮጀክቱ



ስዕል3. የሀብትሽግግር



ስዕል4.የተሻሻለ ኮርማ

በማስገባት፣34 ከብቶችና 61 ፍየሎችን ለማስጠቃት ተችሏል፡፡

**ጥሩ ተሞክሮ፡-** በእህልና ስር ባላቸው ሠብሎች ከፍተኛ የዘር መመለስ ክንውን ምክንያት ለሁለተኛ ዙር ተጠቃሚዎች መሬታቸውን እንዲያዘጋጁ ተደርገዋል፡፡ የዘር ባንክ ኮሚቴዎችም ውጤታማ በመሆን የመጀመሪያውን ግምገማ አልፈዋል፡፡

**ዕቅድ ለቀጣዩ ሩብ አመት**፡- ከታህሳስ እስከ የካቲት 2011

- ለልማት ጣብያ ሰራተኞች ስልጠና መስጠት
- የመስኖ፣ የስራ ስር ዘር ባንክ ፣የሰብል ዘር ባንኮች፣ የእንሰሳት ጤና ኬላ፣ የአርሶአደር ማሰልጠኛ፣ የክትር ስራ ግንባታዎች ማከናወን
- 2ኛ ዙር የሠብልና የስራ ስር ተክሎች ምርትን የማሻሻል ስራ

*This publication has been produced with the assistance of the European Union. The contents of this publication are the sole responsibility of ECC-SADCO, Emdibir Catholic Secretariat, Sodo Catholic Secretariat, and Caritas International Belgium, and can in no way be taken to reflect the views of the European Union.*

caritas international